



# የደብረሰላም መድኃኔዓለም
# የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ አዲስ
# ሕንጻ ቤተክርስቲያን
# አሰሪ ኮሚቴ ድምጽ





# እናስተዋውቃችሁ

## የደብረሰላም መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የህንጻ ግንባታ ኮሚቴ

ኮሚቴው የቤተክርስቲያኑ አባላት በሆኑ ፈቃደኛ ግላሰቦች የተደራጀ ሲሆን 28 የሚሆኑ አባላትን አቅፏል። ዓላማው: አዲሱን የደብረሰላም መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ህንጻ አሰርቶ ማስረከብ ነው። ኮሚቴው ከተዋቀረበት ጉዜ አንስቶ ብዙ ነገሮችን የልዑል እግዚአብሄር ፈቃድ ታክሎበት አከናውኗል። በመጀመሪያ የመተዳደሪያ ደንብ አርቅቆ ተወያይቶበትና ተከራክሮበት ለቤተክርስቲያኑ የአስተዳደር ቦርድ አቅርቦ ካጸደቀ በኋላ በደንቡ መሠረት እራሱን አደራጅቶ ሥራዉን ጀምሯል።

የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ያቀፈው: የኮሚቴውን ሊቀመንበር **ኮረኔል በጋሻው ባልቻን፣ ፀሐፊውን አቶ ዮሃንስ ዘውዴን፣** የ4ቱን ንዑሳን ኮሚቴ ሰብሳቢዎችን እና 1 የቦርድ ተወካዩን ነዉ።

1. **የግንባታ ኮሚቴ** (Design & Construction): **ሰብሳቢ: አቶ መርኃጽድቅ ጥበቡ**
   * የግንባታ ንድፍ ተቋራጮችን አወዳድሮ ለመቅጥር ለምርጫ ያቀርባል።
   * ቤተክርስቲያኑ ምን ዓይነት ይዘት እና መልክ እንደሚኖረው ያጠናል።
   * ለግንባታ የሚያስፈልገውን ወጪ ይተምናል።
2. **የገንዘብ አሰባሳቢ ኮሚቴ** (Fundraising): **ሰብሳቢ: ዶ/ር አሻግሬ አትሬ**
   * የተላያዩ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለሕንጻ ግንባታው የሚውለውን ንዋይ ያሰባስባል።
   * አባላት ለቤተክርስቲያኑ ገንዘብ የሚያስገኙበትን ዘዴ ያመቻቻል።
3. **የሂሳብ ኮሚቴ** (Finance) **ሰብሳቢ: አቶ አንዱዓለም እምሩ**
   * መዋጮ ሰብስቦ ያስገባል።
   * ከተለያዩ ገንዘብ ማስገኛ ዝግጅቶች የተገኘውን ገቢ አሰብስቦ ያስገባል።
   * ብድር እና ሌላ ለግንባታ የሚያስፈልግ ገንዘብ እንዴት እንዳሚገኝ ያጠናል።
   * ለግንባታ የሚያስፈልገውን በጀት ያዘጋጃል።
4. **የሕዝበ ግንኙነት ኮሚቴ** (Public Relations): **ሰብሳቢ: ወ/ሮ ፀኃይ ካሳ**
   * የቤተክርስቲያኑን ግንባታ የተመለከቱ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያቀናብራል፣ ያሰራጫል።
   * በየጊዜዉ ከአባላት አስተያየት እየተቀበለ ለኮሚቴዉ ያቀርባል።

# የመሠረት ድንጋይ የማኖር ሥነ ስርዓት

ጥቅምት ፳፯ ፪፻፱ ዓ ም ወይንም Nov 06, 2016 የጥቅምት መድኃኔዓለምን በዓለ ንግስን ተከትሎ በተያዘው የመሰረት ድንጋይ የማኖር መርኃ ግብር መሰረት የደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተሰቦች ጉዟቸውን አዲስ ወደተገዛው ቦታ አቅንተዋል፡፡ በእለቱም የመሰረት ድንጋዩን ያኖሩ ዘንድ ከቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ መጥተው የነበሩት ብፁዕ አባታችን አቡነ ዳንኤል የምሥራቅ አፍሪካና የድሬደዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በተዘጋጀላቸው ስረገላ በካህናት ፣በሰንበት ትምህርት ቤት፣ በቦርድ፣ በሕንፃ ኮሚቴው አባላት፣ እንዲሁም በብዙ መዕመናን እና በሁለት ሞተረኞች ታጅበው ጉዟቸውን ወደ አዲሱ ቦታ አድርገዋል፡፡ በቦታውም ቀድሞ በመድረስ ይጠባበቅ የነበረው በብዙ መቶዎች የሚቆጠረው የእግዚአብሔር ቤተሰብ ብፁዕ አባታችን ከመላከ ሳለም ቀሲስ ጌታሁን ጋር ቦታው ላይ ሲደርሱ በታላቅ ዝማሬና በእልልታ ነበር የተቀበላቸው፡፡

ለእለቱም የተዘጋጀው ዝማሬና ወረብ በካህናቱ እና በሰንበት ትምህርት ቤቱ አባላት ከቀረበ በኋላ ብፁዕ አባታችን የዕለቱን ቃለ ምዕዳን አስተላልፈዋል፤ መልዕክቱንም እንደጨረሱ በብፁዕነታቸው የመሰረት ድንጋይ ማስቀመጡ ስርዓቱ ተፈፅሟል፡፡

የህንፃ አሰሪ ኮሚቴው የህዝብ ግንኙነት በእለቱ ከታደመት ምዕመናን የእለቱን ታሪካዊነት እና መንፈሳዊ ተግባር በተመለከተ ቃለ መጠይቅ በማድረግ ከዚህ በታች አጠናቅሮታል፡፡

1. እነሆ እግዚአብሄር ፈቅዶ ዛሬ የመሰረት ድንጋዩን አቁመናል ከዚህ በኋላ ደግሞ አባታችን አቡነ ዳንኤል የባረኩትን ቦታ እኛ ልጆቻቸው በርትተን ከፍፃሜ እናደርሳለን፡፡
2. ይህ ቀን ለእኔ ታላቅ ካቴድራል ለመስራት የመሰረት ድንጋይ ያኖርንበት ቀን በመሆኑ ደስታዬ እፁብ ድርብ ነው፡፡
3. በዚህ ታሪካዊ ቀን እግዚአብሄርና ድንግል ማርያምን እናመሰግናለን ::
4. አባታችን አቡነ ዳንኤል መጥተው በመገኘት እንዲህ እንደአሰባሰቡን ለወደፊትም እንዲሁ መድሃኔአለም ያሰባስበን፡፡
5. እግዚአብሄር ይመስገን የሚወረወርብንን ድንጋይ ቤቱን እየሰራንበት ባለ አምስት ጉልላት ቤተ ክርስትያን እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡
6. ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስትያን ትልቅ እርምጃ ነው . ትልቅ ቤተ ክርስትያን በመገንባት ከዚህ በእጥፍ ምእመናን እግዚአብሄርን ለማምለክ እንዲችሉ ይሆናል፡፡
7. ይህ ቦታ ተገኝቶ በመመረቁ በጣም ደስተኛ ነኝ

በማለት የየበኩላቸውን አስተያየት ሰጥተውናል፤ የደብረ ሰላም ምእመናን በዚህ እለት ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ እና ጊዜያቸውን በማስተባበር ቀደም ብለው በቦታው በመገኘት ድንኳን በመጣል፣ ስፍራውን በሰንደቅ አላማ በማስጌጥ፣ እንዲሁም ቦርዱ ባስተባበራቸው ፈቃደኞች እና በህንፃ አሰሪ የገንዘብ አሰባሳቢ ንዑስ ኮሚቴ አማካኝነት የምግብ እና የውሃ ሽያጭ በማድረግ ለሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ማስገንቢያ ይውል ዘንድ ገንዘብ ተሰባስቧል፡፡

በዕለቱ የታየው ህብረትና የምእመናንን ንቁ ተሳትፎ ለተጀመረው መንፈሳዊ ተግባር በበጎ መልኩ ተጠናክሮ ይቀጥል ዘንድ ይበል እንላለን፡፡ ህንፃ ቤተ ክርስትያን ለማነፅ ስንነሳ እግረ መንገዳችንን ለታዳጊ ህፃናትና ወጣት ልጆቻችን ክርስቲያናዊ ስነ ምግባርን፣ አብሮ የማኖርና የመስራት እሴቶችን እንዲያጎለብቱ የሚችሉበትን ሁኔታ ጭምር እያመቻቸንላቸው መሆናችንን ለአንድ አፍታ ልንዘነጋው የማይገባ ጉዳይ ነው፡፡ “ልጅህን በሚሄድበት መንገድ ምራው በሸመገለም ጊዜ ከርሱ ፈቀቅ አይልም" መፅሀፈ ምሳሌ ምዕ 22፥ 6.

እግዚአብሄር አምላክ እንደ ልቤ ብሎ ያከበረው ቅዱስ ዳዊት በዘመኑ ለአምላኩ ቤተ መቅደስ ሊሰራ ቢፈልግ፣ ቤተ መቅደስ የሆነውን የኦርናንን ሰውነት አፍርስሃልና አንተ አትሰራም ነገር ግን ልጅህ ይሰራዋል ብሎ በገባለት ቃል መሰረት፣ ንጉስ ሰለሞን ቃል እንደተገባለት ውብና ያማረ በወርቅ የተለበጠ ቤተ መቅደስ ሰርቷል :: እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ ሆኖ እኛም የተዋህዶ ልጆች በዚህ ትውልድ፣ በዚህ ዘመን እና በዚህ ቦታ ባለ ተራ ሆነን የጌታችንን የመድኃኒታችንን ቤተ መቅደስ ለማነጽ በመታደላችን ክብርና ምሥጋና ለእርሱ ይሁን፡፡
አሜን!